ማኀበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

መስከረም 2000 ዓ.ም.

የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 14

# ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር በኢትዮጵያ

## መግቢያ

እ.አ.አ. በ2002/03 ያልተማከረ የወረዳ አስተዳደር ፖሊሲ በአማራ ፣ ኦሮሚያ ፣ ትግራይና በደቡብ ብሔሮች ፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሚገኙ 430 ወረዳዎች ተግባራዊ ተደረገ። በሚገኘው ተሞክሮ ላይ በመመሥረት ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች ሥራ ላይ እንደሚውል ተገልጿል።

ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር መርሐ ግብር ሥልጣንና ሃላፊነትን ወደ ወረዳዎች በማስተላለፍ መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲን ለማስፈን የታቀደ ነው። ከዚህም ባሻገር ጠንካራ ተቋማዊና አስተዳደራዊ መዋቅር በመዘርጋት ወረዳዎች ቀልጣፋ አገልግሎቶችን እንዲሰጡና ልማትን እንዲያካሂዱ ያስችላቸዋል።

መንግስት ላልተማከለ የወረዳ አስተዳደር በቂ ትኩረት ሰጥቷል። ነገር ግን መርሐ ግብሩ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኗል ለማለት አይቻልም። የሰለጠነ የሰው ሀይል ዕጥረት፣ ውስን የፋይናንስና የበጀት አቅም ፣ ባልተማከለ አስተዳደር አካባቢ የሚታይ የልምድ ማነስና ተፈላጊ የፖሊሲና የማስፈጸሚያ አቅም አለመኖር ዋና ዋና ችግሮች ሆነው ይጠቀሳሉ። እነዚህን ችግሮች በጥልቀትና በስፋት ለመረዳትና ያልተማከለ አሰተዳደርን ተግባራዊነት ለማገዝ የሚችሉ የፖሊሲ ሃሳቦችን ለመጠቆም የማህበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) ከግንቦት 1998 - ኅዳር 1999 ዓ.ም. ድረስ መለስተኛ ጥናት አካሂዷል።

## ጥናቱ የተጠቀመባቸው ዘዴዎችና አላማዎች

ጥናቱ የተካሄደው ከአማራ ፣ ኦሮምያ፣ ትግራይ እና ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ለናሙና በተመረጡ 8 ወረዳዎች ነው። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙ የአራዳ እና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች በናሙናነት በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

ስለ ወረዳዎች የሶሻልና ኢኮኖሚ አጠቃላይ ሁኔታ ፣ አስተዳደር መዋቅርና ይዘት፣ እንዲሁም በጀትንና የገንዘብ አቅምን በተመለከተ መረጃ ተሰብስቧል። በተጨማሪም ከወረዳዎች አስተዳዳሪዎችና የምክር ቤት አባላት ጋር አስተዳደራዊ ጉዳዮችንና የሚያጋጥሟቸውን ዐብይ ችግሮች በተመለከተ ጠቃሚ ውይይቶች ተደርገዋል።

## የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

1. የወረዳዎችን አስተዳደርና መንግሥታዊ መዋቅሮችን ለማሻሻል የሚያግዙ የፖሊሲ ሃሳቦችን ማመንጨት፣
2. የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎቶችን አቅርቦት ለማሻሻልና ለማስፋፋት የሚረዱ ሃሳቦችን መጠቆም፣
3. የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ተሞክሮችንና አዳዲስ አሠራሮችን ማቅረብ ናቸው።

## ያልተማከለ አስተዳደር በኢትዮጵያ ታሪካዊ አመጣጥ

በኢትዮጵያ ስለአልተማከለ አስተዳደር ያለው ልምድ ውስን ነው። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ አገሪቱ ለረጅም ጊዜ በአሃዳዊ አስተዳደር ስትመራ ቆይታለች። በየደረጃው ያሉ አስተዳዳሪዎች በሕዝብ የተመረጡ ሳይሆኑ በማዕከላዊ መንግሥት የተሾሙ ነበሩ። ሥርዓቱ አንድ ወጥ የሆነና ሕዝቡን በልማትም ሆነ በአስተዳደር ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የማያሳትፍ ነበር።

ከንጉሣዊ ሥርዓት ባልተናነሰ መንገድ የደርግ መንግስትም አሃዳዊና አንድ ወጥ አስተዳደር ነበር የሚከተለው። የተዘረጋው አስተዳደር ሕዝብን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያሳትፍ አልነበረም። በየደረጃው ያሉ አስተዳዳሪዎች ተጠያቂነታቸው ለማዕከላዊ መንግስት እንጂ ለሕዝብ እንዳልነበር የቅርብ ትዝታ ነው።

ኢሕአዴግ ስልጣን ከተረከበ በኋላ አገሪቱ ባልተማከለ አስተዳደር

- የማኀበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❋❋❋

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❋❋❋

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❋❋❋

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❋❋❋

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

እንደምትመራ ቃል ገባ:: ሥልጣንና ሃላፊነት በተከታታይ ከማዕከላዊ መንግሥት ወደ ክልል መንግሥታት፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌ አስተዳደሮች በተዋረድ ማስተላለፍ የመንግሥት ፖሊሲ እንደሆነ ተገለጸ:: በረዥም ጊዜ ታሪኳ ሥልጣንና ሃላፊነትን በማዕከል በማከማቸትና በአንድ ወጥ አስተዳደር ለምትታወቅ አገር ይህ ዕርምጃ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል የሚል ተስፋ አሳደረ:: በተግባር ግን ሙሉ በሙሉ የመመሥረቱ ጉዳይ ገና ብዙ ይቀረዋል::

ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ የምትመራው በፌዴራሊያዊ አወቃቀር ሲሆን አምስት የመንግሥት ዕርከኖች አሉት:: እነሱም የፌደራል ፣ የክልል ፣ የዞን ፣ የወረዳና የቀበሌ አስተዳደሮች ሲሆኑ የተሰጣቸው የመንግስት ሥልጣንና ሃላፊነት በሕግ ተወስኗል:: የአወቃቀሩ ዋናው ገጽታ ብሔርን ወይም ብሔረሰብን እና ቋንቋን መሠረት ማድረጉ ነው:: ሕገ መንግሥቱ የፌደራልና የክልል መንግሥታት በዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንደሚተዳደሩና በሕዝብ የተመረጡ ምክር ቤቶች ዋነኛ የስልጣን ምንጭ እንደሆኑ በግልጽ ይደነግጋል:: የሥራ አስፈጻሚ አስተዳደሮችም ለዚሁ ምክር ቤት ተጠያቂ ናቸው:: ራስን በራስ ማስተዳደር፣ የአካባቢን ልማት ማካሄድና መሰረታዊ የሕዝብ አገልግሎቶችን ማቅረብ ሃላፊነት ተሰጥቷቸዋል::

## የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### 1. ያብዛኛው ወረዳዎች የሕዝብ ብዛት ከ100,000 ይበልጣል

በኢትዮጵያ ባብዛኛው የወረዳዎች ሕዝብ ብዛት ከ100,000 በላይ እንደሆነ ታውቋል:: በመስክ ጥናቱ በተገኘው መረጃ መሰረት የብዙ ወረዳዎች የሕዝብ ቁጥር ከ200,000 በላይና ወደግማሽ ሚሊዮን እየተጠጋ እንደሆነ ተደርሶበታል:: ይህ እውነታ በተለምዶ የአንድ ወረዳ ሕዝብ ከ100,000-120,000 ነው የሚለውን አስተሳሰብ ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጐታል::

ከመስክ ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት የወረዳዎች ሕዝብ እያደገ መሄድ አዳዲስ ወረዳዎች እንዲፈጠሩ የሚለውን ጥያቄ እያጠናከረው ነው:: ያዳዲስ ወረዳዎች መፈጠር በጀትን የመመደብ ግዴታና ተፅዕኖ ያስከትላል::

### 2. በወረዳዎች የሚታየው የትምህርት ሽፋን ከፍተኛ ነው

ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር አንዱ ዓላማ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶችን በሰፊው ለማዳረስ ነው:: በሁሉም ወረዳዎች የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሽፋን ከ70 ከመቶ በላይ ደርሶአል:: በተጨማሪ ከጤናና ከንጹህ ውሃ አቅርቦት ጋር ሲነፃፀር የትምህርት ሽፋን ብልጫ ያሳያል::

ከወረዳዎች ጋር ሲወዳደር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአራዳና አዲስ ከተማ ነዋሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የንጹህ ውሃ ፣ የጤናና የትምህርት አቅርቦት ተጠቃሚ ናቸው:: ይህ በገጠር ወረዳዎችና በከተሞች መካከል ያለው የአገልግሎቶች ሽፋን ልዩነት በብሔራዊ ደረጃ ይንፀባረቃል:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት ዕርዳታ ድርጅት (UNICEF, 2006 ) ባደረገው ጥናት የንፁህ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በገጠር አካባቢዎች 11 በመቶ በከተሞች ደግሞ 81 በመቶ እንደሆነ ያሳያል::

### 3. የመልካም አስተዳደር ተቋማዊ ብቃትና አደረጃጀት ብዙ ይቀረዋል

የወረዳ አስተዳደራዊ መዋቅር የሥራ አስፈጻሚ ፣ በሕዝብ የተመረጠ ምክር ቤት እና ብዙ ቋሚ ሠራተኞችን ያቀፈ ነው:: የወረዳው ምክር ቤት በዓመት 4 (አራት) ጊዜ እየተሰበሰበ በጀትና የልማት ዕቅድ ያጸድቃል:: ከሌሎች አገሮች ልምድ በመነሳት ይህ አሠራር ደሞክራሲንና ተጠያቂነትን አያጐለብትም:: ወረዳውን በቋሚነት የሚያስተዳድር ሥራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ (ካቢኔ) አለ:: ኮሚቴው ከ 11-13 የሚደርሱ አባላት አሉት::

የወረዳ ምክር ቤት አባላት ለአገልግሉታቸው የደሞዝ ክፍያ የላቸውም:: ሙሉ ደሞዝተኛ የሆኑት የአስፈጻሚ ኮሚቴ (ካቢኔ) አባላት ብቻ ናቸው:: ይህ አካሄድ በሁለቱ ግንኙነት ላይ ምን ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ለማወቅ ጥናት ያስፈልጋል:: አሁን በሥራ ላይ ያሉት አባላት እ.አ.አ. በ2002/03 በተካሄደው ብሔራዊ ምርጫ ወቅት የተመረጡ ናቸው::

### 4. በወረዳዎች አስተዳደር የሴቶች ተሳትፎ በጣም አናሳ ነው

የሴቶች ተሳትፎ በወረዳዎች አስተዳደር በጣም ያነሰ ነው:: በመስክ ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ አንድ ወረዳ ብቻ 2 የሴት አባላት ሲኖሩት በሌሎች ሰባት ወረዳዎች ከ13 የሥራ አስፈጻሚ አባላት ውስጥ 1 የሴት አባል ያለበት ወረዳ አንድ ብቻ ነው::

በአንጻሩ የሴቶች ተሳትፎ በወረዳ ምክር ቤቶች የተሻለ ሁኔታን ያሳያል:: በዚህም መሠረት ከወረዳ ምክር ቤቶች አባላት ውስጥ የሴት አባላት ቁጥር በአንድ ወረዳ 43 በመቶ ፣ በሌላው 56 በመቶ ሲሆን ፣ በሌሎች ወረዳዎች በአማካኝ ከ24 እስከ 44 ከመቶ እንደሆነ ታውቋል::

### 5. በወረዳዎች የአስተዳደር ሠራተኞች ከፍተኛ የሙያ ብቃት ማነስ ይታያል

በቂ ትምህርትና ልምድ ያለው የሰው ኃይል እጥረት ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ሥር እንዳይሰድ ዋነኛ ችግር ነው:: የወረዳ አስተዳዳሪዎችና ምክር ቤት አባላት ቁልፍ የውሳኔ መስጠት ሚናና መልካም አስተዳደር ማስፈን ሃላፊነት ቢሰጣቸውም ያላቸው ብቃት ለዚህ አይመጥንም::

በአብዛኛዎቹ መምህር የነበሩ ናቸው ፣ ስለዚህም በአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚረዳ ሥልጠና አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም::

ብዙዎች ወረዳዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቋሚና

የኮንትራት አስተዳደር ሠራተኞች አሏቸው፡፡ የነዚህ ሠራተኞች ዋና ሃላፊነቶች አገልገሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ለሕዝብ ማበርከትና በአካባቢው የኢኮኖሚና የሶሻል ዕቅዶችን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ከመስክ በተገኘ መረጃ መሠረት ብዙዎች ሠራተኞች በቂ ትምህርት ወይም ሙያዊ ልምድ የላቸውም ፣ የሚከፈላቸውም ደሞዝም በጣም አናሣ ነው፡፡ ስለሆነም ለሥራ ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጐት ዝቅ ብሎ ይታያል፡፡ በመሠረታዊ ሥራ አመራር ሙያ ፣ በዕቅድ አወጣጥና በፋይናንስና በጀት አስተዳደር ያላቸው ብቃት በጣም ውስን ነው፡፡ ስለሆነም በበጀት አዘገጃጀት ፣ በመሠረታዊ የሂሳብና ገንዘብ አስተዳደር ሙያ ፣ እንዲሁም በአነስተኛና ጥቃቅን ፕሮጀክቶች አቀራረጽ ፣ ክትትልና ቁጥጥር በቂ ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 5. የአንድ ፖለቲካ ፖርቲ የበላይነት ይታያል

ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ለመዘርጋት ነፃና በውድድር ላይ የተመሠረተ የፖለቲካና ኢኮኖሚ መድረክ ወሳኝ ነው፡፡ ነፃ በሆነ የፖለቲካ መድረክ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋንያን ሃሳባቸውንና አማራጮችን በነፃ ማንሸራሸር መቻል ላልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ሥር መስደድ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፡፡

በብዙ አገሮች እንደሚታየው በኢትዮጵያም የፖርቲ ፖለቲካ በአካባቢ አስተዳደር ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ በወረዳ አስተዳደር ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ በወረዳ ደረጃ የሚታየው ፖለቲካና መልካም አስተዳደር ውድድር የተሞላበት ነው ብሎ ለመደምደም አዳጋች ነው፡፡ በተገኘው መረጃ መሠረት የገዢው ኢሕአዴግ ፖርቲ አባል መሆን በወረዳ አስተ ዳደር ለመመረጥ ወይም ለመሾም ዐብይ መመዘኛ ነው፡፡ በወረዳ ሥራ አስኪያጅ አባልነት የሚያገለግሉትና ዋና ዋና ቢሮዎችን በሃላፊነት የሚቆጣጠሩት በሙሉ የገዢው የኢሕአዴግ ፖርቲ አባላት መሆናቸው በጥናቱ ታውቋል፡፡ አንድ ፖርቲ በብቸኝነት የፖለቲካ መድረኩን መቆጣጠር ለዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መጐልበት አይረዳም፡፡

የወረዳ አስተዳደር ከአንድ ብቸኛ ፖርቲ በተውጣጡ ሰዎች መሞላቱ ጥቅምና ጉዳት አለው፡፡ የገዢው ፖርቲ አስተዳደሩን በብቸኛነት መቆጣጠር መርሐ ግብሮቹንና ፖሊሲዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡ በሌላ ረገድ ግን የወረዳ አስተዳዳሪዎችና ሃላፊዎችን ለክልልና ለፌደራል መንግስት ያላቸውን ተጠያቂነት ያጠናክረዋል፡፡ ለህዝቡ ፍላጐትና ጥቅም ያላቸውን (የሚኖራቸውን) ተጠያቂነት ያዳክመዋል፡፡ በይበልጥም ደግሞ የአንድ ብቸኛ ፖርቲ የበላይነት በወረዳ ደረጃ ያለውን የፖለቲካ መድረክ ያጠባል፡፡ ከገዢው ፖርቲ ውጭ ያሉ ተዋንያን ወይም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲዎች በነፃ እንዳይንቀሳቀሱና ለሕዝቡም አማራጮችን እንዳያቀርቡ ሊያግዳቸው ይችላል፡፡

## 6. የወረዳዎች በጀት ባብዛኛው ለደሞዝና ለአስተዳደር ወጪ ይውላል

ወረዳዎች ባጠቃላይ ከፍተኛ ብዛት ያለው የሰው ሀይል ያስተዳድራሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ ከየወረዳዎች በጀት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ለደሞዝና ለተለያዩ አስተዳደር ወጪዎች ይውላል፡፡ ከመስክ በተገኘው መረጃ መሠረት በአማካይ 91 ከመቶ የሚሆነው የወረዳዎች በጀት ለደሞዝና ለአስተ ዳደር ወጪዎች ይውላል፡፡ ይህ ሁኔታ ወረዳዎች ልማትን ለማካሄድና የአገልግሎት ሽፋን ለማስፋት የሚያደርጉት ጥረት የተፈለገውን ያህል እንዳይሆን አድርጐታል፡፡

## 7. የፌዴራል ፣ ክልል ፣ ዞን ፣ ወረዳና ቀበሌ መንግሥታዊ አካሎች የሥልጣን ክፍፍልና ግንኙነት ግልጽ አይደለም

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ አምስት የመንግስት ዕርከን ባለው አወቃቀር ትመራለች፡፡ እነሱም፡- የፌደራል ፣ ክልል ፣ ዞን ፣ ወረዳና ቀበሌ አስተዳደሮች ናቸው፡፡ በሕገ-መንግሥቱ የያንዳንዱ ሥልጣንና ሃላፊነትም ተደንግጓል፡፡ በተግባር ግን ሲታይ ግንኙነቶችና የሃላፊነት ክፍፍሎች አካባቢ ችግሮች ይታያሉ፡፡

ለምሳሌ ሕገ-መንግሥቱ የወረዳ አስተዳደሮች ነፃና የራሳቸው የሆኑ ሥልጣንና ውሳኔ የመስጠትና የመተ ግበር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ በተግባር ግን የክልልና የፌዴራል መንግሥታት እንደሚቆጣጠሯቸውና በውስጥ ጉዳያቸውም በተደጋጋሚ ጣልቃ እንደሚገቡ ይታያል፡፡ ይህ እነዚህ የመንግስት አካላት ለሕዝብ ያላቸውን ተጠያቂነት እንደሚያቀጭጨው ግልጽ ነው፡፡

## 8. የወረዳ አስተዳደሮች ከራሳቸው የሚያገኙት የበጀት ድርሻ በጣም ውስን ነው

ወረዳዎች አብላጫውን በጀታቸውን የሚያሟሉት ከክልል መንግሥታት ከሚያገኙት ጥቅል የበጀት ዝውውር ነው፡፡ ዝውውሩ አራት መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ እነሱም የሕዝብ ብዛት 55 በመቶ ፣ የልማት መለኪያ 25 በመቶ ፣ የራስ ገቢ መጠን 15 በመቶና የድህነት መለኪያ 10 በመቶ ናቸው፡፡ እነዚህ መመዘኛዎች በየጊዜው እንደሚለዋወጡ ታውቋል፡፡ የተ ዛወረላቸውን በጀት ወረዳዎች ለተለያዩ መርሐ ግብሮች ማለትም ለትምህርት ፣ ለጤና ፣ ለገጠር ልማት ወዘተ የማከፋፈል ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

# ከጥናቱ የመነጩ ዐቢይ የፖሊሲ ፍሬ ሃሳቦች

## 1. የፖለቲካ መድረክ መጥበብ ሁኔታ

ከመስክ ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት ገዢው ኢሕአዴግ ፖርቲ በወረዳ አስተዳደር ዋነኛና ብቸኛ ተዋናይ ነው፡፡ በመሆኑም ሌሎች ከገዢው ፖርቲ ውጭ ያሉ ተዋ ንያን በተለያዩ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዩች እንዳይሳተፉና የፖለቲካ መድረኩ እንዲጠብ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የወረዳ ሥራ አስፈፃሚና አብዛኛው የምክር ቤት አባላት የገዢው ፖርቲ አባል መሆናቸው የፖርቲውን ብቸኛ ተዋናይነት ያሳያል፡፡ ሁሉንም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋንያንን ሊያሳትፍ የሚችልና ውድድር የተሞላበት የፖለቲካ መድረክ አለመኖር

የተጀመረውን የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሊያዳክመው ይችላል:: የአንድ ፖርቲ ብቸኛ ተዋናይ መሆን የወረዳን የራስ በራስ የአስተዳደር ሥልጣን ይሸረሽራል ፣ አልፎም መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ከሕዝቡ/ሕብረተሰቡ ይልቅ ለበላይ አካላት ያላቸውን ተጠያቂነት ያጠናክራል::

## 2. የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች አቅርቦትና ፍላጐት አለመመጣጠን

ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ፣ ማለትም ትምህርት ጤና፣ ንጹህ ውሃ ፣ ወዘተ አቅርቦት እንዲጨምር ይረዳል:: ነገር ግን እያደገ የመጣውን የሕዝብ ፍላጐት በበጀትና የሰው ሃይል እጥረት ሳቢያ ወረዳዎች ለማሟላት ተስኗቸዋል:: መፍትሔ የሚሆነው ከክልል መንግሥታት ወደ ወረዳዎች በየጊዜው የሚተላለፈውን በጀት መጨመርና በአካባቢው የሚገኘውን የገንዘብ ፣ የቁሳቁስና የሰው ኃይል በማስተባበር (በማቀናጀት) የልማት ፕሮጀክቶችንና አገልግሎቶችን ተግባራዊ ማድረግ ነው::

## 3. ያለበቂ በጀት ለወረዳ አስተዳደሮች ስለሚሰጡ ተግባራትና ሃላፊነቶች

በመስክ ጥናት ወቅት በቂ በጀት ሳይመደብላቸው ተግባሮችና ሃላፊነቶች ለወረዳ አስተዳደሮች ከክልል መንግስታት እንደሚተላለፍ በተደጋጋሚ ተገልጿል:: በቂ ገንዘብ ፣ የሰው ሀይልና መሣሪያዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሕዝብን ፍላጐት ማርካት አይቻልም:: በተደጋጋሚ የህዝብን ጥያቄ ለመመለስ አለመቻል ሕብረተሰቡ በአስተዳዳሪዎችና ሃላፊዎች ላይ እምነት እንዲያጣ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

## 4. በወረዳ ደረጃ ያለው የአቅም ውሱንነት

በግልጽ ከሚታየው የበጀትና የገንዘብ ችግሮች ባልተናነሰ መንገድ የሰለጠነና ባለሙያ ሠራተኛ እጥረት የወረዳዎችን የሥራ እንቅስቃሴ ያገተ መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል:: በተጨማሪም የተለያዩ መሣሪያዎችና መገልገያዎች ፣ ማለትም የቢሮ ዕቃዎች ፣ ኮምፒውተሮች ፣ የማተሚያና ማባዣ መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች ፣ ወዘተ በበቂ ሁኔታ አለመቅረብ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ችግሮች ናቸው:: የችግሮች ስፋትና ጥልቀት እንደየወረዳዎች ይለያያሉ:: ሌላው ዋነኛ ችግር መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ያልተሟሉባቸው ወይም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙባቸው ወረዳዎች ቁጥር ብዙ መሆን ነው:: በነዚህ ወረዳዎች ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑ ባለሙያዎች ማግኘቱ አዳጋች ሆኗል:: ባለሙያዎች ወደ እነዚህ ወረዳዎች ሄደው እንዲያገለግሉ ከተፈለገ የክልል መንግሥታት የተሻለ ከፍያና ጥቅማጥቅሞችን የሚሰጥ አሠራር መጀመር ግድ ይላቸዋል::

## 5. አስፈላጊ የሕግና የክትትል ሥርዓት አለመኖር

ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ለመተግበር አስፈላጊ የሕግና የክትትል ሥርዓት አለመኖር በጥናቱ ግልጽ ሆኖአል:: የክልል ሕገ-መንግሥቶች መደበኛ ሥልጣንና ሃላፊነቶች ይዘረዝራሉ ፣ ነገር ግን ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ፣ ለምሳሌ የወረዳና የክልል መንግሥታት ሃላፊነቶችና የሥልጣን ገደቦች ወይም ወረዳዎች በራሳቸው በጀትና ፋይናንስ ለማስተዳደር ያላቸውን ሥልጣን በግልጽ አያስቀምጡም::

አንዳንድ ክልሎች በዚህ ጉዳይ አካባቢ የተወሰነ እንቅስቃሴ አድርገዋል:: ለምሳሌም የአማራ ክልል ያዘጋጀው የወረዳ ገንዘብና በጀት አስተዳደር ሕግ ረቂቅ ሊጠቀስ ይችላል:: ሁሉም ክልሎች ይህን ዓይነቱን አሠራር መጀመር እንዳለባቸው ግልጽ እየሆነ መጥቷል::

## 6. ሥልጣንና ሃላፊነትን ለቀበሌ አስተዳደሮች የማስተላለፍ አስፈላጊነት

የቀበሌ አስተዳደሮች የመጨረሻው የመንግስት እርከን ናቸው:: በዚህም ሳቢያ በቂ ሥልጣን፣ የአስተዳደር ብቃትና የገንዘብና የቁሳቁስ አቅም ሊኖራቸው ይገባል:: ነገር ግን የቀበሌ አስተዳደሮች በቂ ሥልጣን እንደሌላቸውና በከፍተኛ ደረጃ የገንዘብና የቁሳቁስ ችግር እንዳለባቸው በጥናቱ ተረጋግጧል:: በዚህም ሳቢያ የወረዳ አስተዳደሮች ትዕዛዝ አስፈጻሚ እንጂ ራሳቸውን ችለው በመንቀሳቀስ የሕዝብን ጥያቄና ችግር ለመመለስ አልቻሉም:: ከሁሉም በላይ የቀበሌ አስተዳደሮች ከፍተኛ የበጀት እጥረት እንዳለባቸውና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያቸውም በወረዳ አስተዳደሮች ጥብቅ ቁጥጥር እንደተገታ ጥናቱ ጠቁሟል::

**ምህረት አየነው (ዶ/ር)**

**ዋና ምንጭ:-** Taye Assefa and Tegegne Gebre-Egziabher, eds. 2007. *Decentralization in Ethiopia*. Addis Ababa: FSS.

**Acknowledgement & Disclaimer**

*This document has been produced with the financial assistance of the European Union. The contents of this document are the sole responsibility of the author and can under no circumstances be regarded as reflecting the position of the European Union.*

**አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
**ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79**
**ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et**